## *የታጋይነት ስነምግባር የማይገባው ቡድን ከጥፋት መንገድ የሚመለሰው መቼ ይሆን?*

*(ከኦነግ ኢ.ንፎ ዴስክ)*

ከሶስት ኣመታት በፊት ከኦነግ ተለይቶ ራሱን *"የለውጥ ኣራማጅ"* ብሎ የሰየመው ቡድን እስከ ዛሬ ድረስ የተከተለውን የጥፋት ጎዳና ሁሉም እየታዘበ ነው። ይህ ቡድን ከ2008 ጀምሮ በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ላይ የፈፀመውን ወንጀል ዘርዝሮ መጨረስ ኣስቸጋሪ ነው። ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ግን የግድ ይሆናል። ቡድኑ ደቡብ ኦሮምያ በሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት መሃል ሁከት ቀስቅሶ ታጋዮቹን ደም ኣፋስሷል። ለትግል ኣላማ ከቤታቸው የወጡ ልጆች ከነፃነት ትግሉ ተስፋ ቆርጠው ለጠላት እጃቸውን እንዲሰጡ መርቷል። ኣንዳንድ የቡድኑ ከፍተኛ ኣመራር ኣባላት ጠላትን ለመታገል ከቤታቸው የወጡትን የኦሮሞ ወጣቶች እስከነትጥቃቸው ኣሰልፈው ለወያኔ ኣስረክበዋል። ለራሳቸውም በጠላት መገናኛ ብዙሃን ላይ ብቅ ብለው በሰጡት ኣስነዋሪ መግለጫ ለነፃነት ትግሉ ያላቸውን ጠላትነት ኣስመስክረዋል። በዚህም የኦሮሞ ህዝብን ኣንገት ኣስደፍተው ጠላትን ኣስፈንድቀዋል። በሌሎች ኣካባቢዎች ደግሞ በሰራዊቱ መሃልና በነባር የድርጅቱ ኣባላት መካከል በቀሰቀሱት ሁከት የብዙዎች ህይወት እንደዋዛ እንዲጠፋ ምክንያት ሆነዋል። ይህም ሳይበቃቸው ከድርጅቱ ህጋዊ ኣካሄድ ውጪ *"የኦነግ ማኒፌስቶ"* ያሉትንና ከኦነግ ነባር የፖለቲካ ፕሮግራም ጋር የሚፃረር ሰነድ ኣርቅቀው በፖለቲካ ኣላማ ላይ የኦሮሞ ታጋዮችን ግራ ኣጋብተው ለማባላት ጥረት ኣድርገዋል። ይህ ሁሉ እንግዲህ ቡድኑ በኦሮሞ ህዝብ ብሄራዊ የነፃነት ትግል ላይ ከፈፀማቸው በርካታ ወንጀሎች መካከል በጥቂቱ የሚጠቀስ ነው።

ቡድኑ እነኚህን ወንጀሎች ከፈፀመ በሁዋላም ቢሆን ለነፃነት ትግሉ ያለውን ጠላትነት በተቻለለት መንገድ ሁሉ ከማስመስከር ኣልቦዘነም። መስሎኣቸው ከቡድኑ ጋር ተሰልፈው የነበሩና ውለው ኣድረው መሰሪነቱን ተገንዝበው መስመራቸውን ያስተካከሉ በርካቶች ናቸው። በመሆኑም ቡድኑ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች ስብስብ ብቻ ወደ መሆን ከወረደ በሁዋላም ቢሆን ግን ኣይኑን ከፍቶ ከተዘፈቀበት የጥፋት ኣረንቂዋ ለመውጣት ፍላጎት ኣላሳየም። በኣቢሲኒያ (ሓበሻ) ወገኖች በተሰጠው ተልእኮ መሰረት የኣንድ ኦሮሞ ታጋይ ልጆችን በፖለቲካ ኣመለካከት ከፋፍሎ ለማቃቃር ያለውን እቅድ ገቢራዊ ለማድረግ ዛሬም እየደከመ ነው። እስካሁን በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ጎራ ውስጥ በፈፀማቸው ወንጀሎች ሳቢያ በሰፊው የኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ከመተፋቱ የተነሳ ፊቱን ወደ ባእዳን ጉያ ሲመልስ እያየን ነው። "ኦነግ" የሚለውን ድርጅታዊ ስም እንደ ንግድ ምልክትነት (trade mark) በመጠቀም ከኣቢሲኒያዉያኑ ጋር የፖለቲካ ኮንትራት ውል ለመፈራረም ሲሞዳሞድ ይታያል። ይህ የጥፋት ቡድን ኣቢሲኒያዉያን ፖለቲከኞች ደካማና በቀላሉ የሚጠቃላቸውን ኦነግ ለማየት ያላቸውን የረጂም ጊዜ ህልም እውን ለማድረግ የኦነግን የፖለቲካ ፕሮግራም እየተዳፈረ ነው። የታጋይነት ስነምግባርም ሆነ የኦሮሞነት ባህላዊ ምግባር የጎደለው ቡድን ለመሆኑ ይህ ኣንድ ኣብነት ነው።

ኣንድ ሃቅ ግን ሊታወቅ ይገባል። በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ውስጥ እንደ ድርጅት ኣዲስ የፖለቲካ ኣመለካከት ለመገምገም ሆነ ኣዲስ ኣይነት የፖለቲካ ኣላማ ካስፈለገ በኣግባቡ ከስምምነት ላይ ደርሶ የማወጁ ሃላፊነት ትላንት ከትግራዩ ወያኔ ጉያ እንዲወጣ የተደረገና ዛሬ ከኣማራ የፖለቲካ ጉያ ውስጥ ለመሸጎጥ የተመቻቸ ቡድን ሊሆን ኣይችልም! ይህን ለማድረግ መብቱም ሆነ ሞራሉ ያለው ህጋዊ ኣግባብነቱን ያሟላ ጠቅላላ ጉባኤ (Gumii Sabaa) ብቻ ነው። ጠቅላላ ጉባኤውም ቢሆን ይህን ለማድረግ የሚችለው የኦሮሞ ህዝብን የሚያሳምንበት ተጨባጭ ምክንያት ሲኖረው ብቻ ነው። የኦነግ የፖለቲካ ፕሮግራም ማለት እንዲህ ያለው ጋጠወጥ ቡድን ማስታወሻ ደብተሩ ይመስል ብድግ ብሎ በፈለገበት ሰኣት የሚሰርዘውና የሚደልዘው ርካሽ ሰነድ ኣይደለም።

ኦነግ በትግል ታሪኩ ውስጥ በትውልድ ኦሮሞ እየተባሉ ከባእዳን ጋር ተሰልፈው የጥቃት ሰይፋቸውን እሱ ላይ የመዘዙ በርካታ ወገኖችን ታዝቧል። በደርግ ዘመን እነመኢሶንና ኢህኣፓ የኦነግን ህልውና ለመፈታተን ሞክረው ነበር። በወያኔ ዘመን ደግሞ ኦፒዲኦ በጣውንትነት የተጠፈጠፈው የኦነግን ሃያል የትግል ሚና ከተቻለ ለመደምሰስ ካልሆነም ለማዳከም ታልሞ ነበር። ኦነግ ግን እነዚህን ጥቃቶች ሁሉ በድል እየቀለበሰ እነሆ እዚህ ደረሰ። ዛሬም ሆነ ነገ ለስም ከኦሮሞ መወለዳቸውን እየነገሩን በኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅትነት ራሳቸውን ሰይመው ለባእዳን ጥቅም የሚሰለፉ እንደማይታጡ ኣይጠረጠርም። እነዚህም ቢሆኑ ታዲያ ቀደም ሲል እንደተጠቀሱት ሃይሎች ሁሉ መጨረሻቸው ኪሳራ መከናነብ ብቻ ይሆናል።

ዛሬ ኦነግ በተለያዩ ኣንጃዎች ተከፍሏል እያሉ የሚያራግቡ ወገኖች መኖራቸው ኣያስገርምም። ሃቀኛው ኦነግ ማለት የቱ ነው እያሉም ጥያቄ የሚያቀርቡ ኣልታጡም። ሃቀኛው ኦነግ ማለት ግን ያው ኣንድ ኦነግ ብቻ ነው። እውነተኛው ኦነግ ማለት ደግሞ የቱ እንደሆነ ኣይደለም የኦሮሞ ህዝብ የወያኔ መንግስት ራሱ በትክክል ይረዳል። ኦነግን እንደ ጦር የሚፈራው ወያኔ በኦነግነት የሚያውቀው ዘወትር ከእንቅልፍ የሚያባንነውን ኣንድ ብቸኛ ኦነግንና ኣመራሮቹን ብቻ ነው። ወያኔ ለዚህ ኣመራር የተለየ እውቅና ለመስጠት ፈልጎ ኣይደለም። በሁሉም ኣቅጣጫ ጨምድዶ ይዞት ኣላላውስ ያለው ይሄው ኣመራር መሆኑን በትክክል በመገንዘቡ እንጂ። ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ስርኣቱ በየጊዜው እየተወነ የሚያቀርበውን ፀረ ሽብር ተብዬ ርካሽ ድራማውን መመልከቱ በቂ ነው።

በኦነግ ስም ከኣቢሲኒያዉያኑ የፖለቲካ መደብር ገብቶ የሚነግደው ከላይ የተጠቀሰው “ለውጥ ኣራማጅ” ነኝ የሚለው ቡድን በሶስት ኣመታት ህይወቱ ኣንዲት ጠጠር እንኳዋን ወያኔ ላይ ከመወርወር ይልቅ ባእዳንን ኣስፈንጥዞ ኦሮሞን ኣንገት የሚያስደፋ ኣፍራሽ ተግባር ላይ መሰማራቱን ደግሞ ደጋግሞ እያስመሰከረ ይገኛል። ለጥፋት ኣላማ የተሰባሰበው ይህ ቡድን በስሩ የተሰለፉትንም ሳይቀር እየበተነ በዜሮ እስከሚቀር ድረስ ኣደብ የሚገዛም ኣይመስልም። የቡድኑ የፖለቲካ ፍልስፍና ሸንኩርት ከመላጥ ስልት የተለየ ኣይደለም። የገዛ ኣካሉን እንደ ሸንኩርት እየላጠ እስከሚጨርስ ድረስ መቆሚያ ኣይኖረውም። የሰፊው የኦሮሞ ህዝብ መሪ ድርጅትነት ሚና ያለውን ኦነግን የሚያክል የኣመራር ሃላፊነት መሸከም ቀርቶ የገዛ ኣካሉን እንደ ሸንኩርት ልጦ

*ጨርሶ በልጣጭነት ከመቅረት ራሱን ሊያድን ኣልቻለም። ከቡድኑ ጋር ሄደው ዋል ኣደር ሲል መሳሳታቸውን ተረድተው የተመለሱትና ዛሬም እየተመለሱ የሚገኙ ወገኖች ሁሉ የዚህ ሃቅ ምስክሮች ናቸው።*

*ያም ሆነ ይህ የኦሮሞ ህዝብን የነፃነት ትግል ጎራ መልሶ የማጠናከር ሃላፊነት የሁላችንም ነው። ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ከድርጅቱ ራሳቸውን ያገለሉ ወገኖች ስህተታቸውን ተገንዝበው ኦነግና ህዝባችን ለትግሉ ስኬታማነት እየከፈሉ ለሚገኘው ዘርፈ ብዙ መስዋትነቶች እውቅና ሲሰጡና ድጋፋቸውን ሲያበረክቱ ነው። በኦነግ ስም ራሱን እየጠራ የኣቢሲኒያዊ ድርጅት ተለጣፊ ለመሆን የታጨው ቡድን በሚቀጥለው መንግስት ውስጥ ሌላ ኦፒዲኦ ሆኖ ብቅ ለማለት ከሆነ ኣላማው፣ በኦሮምያችን ዘመኑ ኣዳዲስ ኦፒዲኦዎችን ለማየት የሚፈቅድ ባለመሆኑ ውጤቱ ኪሳራ ብቻ መሆኑን እናስገነዝባለን።*

*ግንቦት ሰባት የሚሰኘው ድርጅትም በቁጥር ጥቂት ከሆኑና ራሳቸውን የኦነግነት ለምድ ኣልብሰው በኦሮሞ የነፃነት ትግል ጎራ ላይ ወንጀል ለሚፈፅሙ ግለሰቦች የድርጅትነት እውቅና የመስጠት መብት የለውም። ይህ ኣቢሲኒያዊ ድርጅት ሃቀኛውን ኦነግ በሚገባ እያወቀ፣ ለጥፋት ኣላማ የተሰማራውን ቡድን በድርጅትነት ስም እየካበ በምርኩዝነት መጠቀሙ ለኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ውድቀት ያለውን ምኞት ያሳያል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ይህ ድርጅት የኦሮሞ ህዝብን ኣንድነት ለማዳከም የነደፈውን ፖሊሲ በማስረጃ ኣስደግፈን ለማጋለጥ ባንቸኩልም ወቅቱ ሲደርስ እንመለስበታለን። ትላንት ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ ትግል ለማጨናገፍ ካለው ኣላማ ጥቂት ሆዳደር ግለሰቦችን ኣሰባስቦ ኦፒዲኦ የሚል ስም ኣውጥቶላቸው ኦነግን ሊያዳክም ጥረት እንዳደረገው ሁሉ ይሄኛው ኣቢሲኒያዊ ድርጅትም ጥቂት የከሰሩ ግለሰቦችን በመሳሪያነት የመጠቀም ዝንባሌ ማሳየቱ ገና ከጅምሩ የውድቀት መስመር መከተሉን ያስገነዝባል። ስለሆነም ግንቦት ሰባት ለሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ትግል ተገቢ ክብር የሚሰማው ከሆነ ከኦነግ ድርጅታዊ መዋቅር የተተፋውን ቡድን እንደ መሳሪያ ከመጠቀምና የኦሮሞ ታጋዮችን ኣንድነት ለመሸርሸር ከተያያዘው ሴራ ባስቸኩዋይ እንዲገታ ኣበክረን እናሳስባለን።*

*የኦነግ ኢንፎ ዴስክ*